# የማህበራዊ ኃላፊነት ፖሊሲ

ቀን ፡ ግንቦት 01 ፥ 2016

Allied Gold Corporation (“Allied” ወይም "ኩባንያው") የማህበራዊ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ለመስራት ቁርጠኛ በመሆኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በአመኔታ ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን መገንባት እና ማስቀጠል፣ እንዲሁም ለተቀባይ ማህበረሰባችን የረዥም ጊዜ እድገት አስተዋጽዖ የሚያደርግ የጋራ እሴት ማመንጨት የዚህ ቁርጠኝነት አስፈላጊ ገጽታ እንደሆነ ይገነዘባል።

ኩባንያው፣ በዚህ ፖሊሲ አማካኝነት የሚከተሉትን ለማድረግ ቁርጠኛ ነው፡-

- የማህበረሰብ እሳቤዎች በሁሉም የኩባንያው ገጽታዎች ውስጥ መካተታቸውን የሚያረጋግጥ የኩባንያ ባህልን ለማስተዋወቅ።
- እንደ ዝቅተኛ የመመዘኛ ስታንዳርድ ተጠያቂ የምንሆንባቸውን ሁሉንም ተፋጻሚነት ያላቸውን ሕጎች እና ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን ለማክበር።
- በኩባንያው አፈጻጸም ውስጥ ቀጣይነት ያለው መሻሻልን ለመደገፍ የአስተዳደር ስርዓትን ለማዘጋጀት እና ለማስቀጠል።
- ለኩባንያው ማህበራዊ አፈጻጸም አመራርን እና ተጠያቂነትን ለማሳደግ።
- ከማህበረሰብ ጋር የተገናኙ ዓላማዎችን እና ዒላማዎችን ማውጣት እና በመደበኛነት ለመገምገም።
- የማህበረሰቡን ዓላማዎቻችን ለማሳካት በቂ ሀብቶችን ለማቅረብ።
- የኩባንያ እና የጣቢያ ደረጃ ማህበራዊ አፈጻጸምን በመደበኛነት ለመገምገም።
- ሁሉም ሰራተኞች እና ተቋራጮች የየራሳቸውን ኃላፊነት እንዲገነዘቡ ለማድረግ እና ቀጣይነት ባለው ትምህርት እና ስልጠና እውቀታቸውን የሚያሳድጉባቸውን እድሎችን ለመስጠት።

***ተሳትፎ***

- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ምክክር እና ተሳትፎ ላይ በመመሥረት በማዕድን ቁፋሮው ዘመን ሁሉ ክፍት እና ግልጽ፣ አካታች እና ባህላዊ አግባብ ባለው ተሳትፎ ግንኙነቶችን መገንባት እና ማስቀጠል።
- በማህበረሰቡ ውስጥ ለመኖራችን ሰፊ የማህበረሰብ ድጋፍ ለማግኘት እና ለማቆየት መሥራት።
- የማህበረሰቡን ጉዳዮች ወጥነት ባለው እና ግልፅ በሆነ መንገድ ለመለየት እና ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብ ዘዴን ማቋቋም እና ማስቀጠል።

***የለውጥ/ተጽዕኖ አስተዳደር***

- የማህበረሰብ መብቶችን፣ ፍላጎቶችን፣ እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ባህልን፣ እና ከተፈጥሮ ሃብቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ማክበር።

- ለውጣችን/ተጽኖአችን በምንመራበት ጊዜ፣ የሥራ እንቅስቃሴያችንን በምናከናውንበት አከባቢ ውስጥ  የሚካሔድ  የዕደ ጥበብ ወይም አነስተኛ የማዕድን ማውጣት ሥራ ሲኖር  ወደ ንብረቶቻችን ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ መድረስ መቻላችንን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ስልቶችን ለመለየት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መሥራት።

- የማህበረሰቡን ስጋቶች እና እድሎች በንቃት መለየት እና መገምገም፣ ከዚያም እነዚህን ምልከታዎች ከኩባንያው ተግባራት ጋር ማዋሃድ።

- አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ እና ከተቻለ ለማካካስ እና አወንታዊ ተፅእኖዎችን ለማሳደግ የአደጋ ቅነሳ ተዋረድ መዋቅርን መተግበር።

- ያለፈቃድ ሰፈራን ማስወገድ እና ማስቀረት በማይቻልበት ሁኔታ ደግሞ መልሶ ሰፈራን እና የኑሮ ደረጃን በነበረው ወይም በተሻለ ሁኔታ የሚያቋቁም ጥሩ ተሞክሮን መተግበር።

- የባህል ቅርሶችን ማክበር።

***አዎንታዊ ጥቅሞች***

- የሥራ ቅጥርን እና ግዥን ለምንሠራበት ሀገር እና ማህበረሰቦች ቅድሚያ መስጠት።

- ለተቀባይ ማህበረሰቦች ዘላቂ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያስገኙ ተነሳሽነቶችን/ውጥኖችን ማሳደግ እና ድጋፍን መተግበር።

ይህ ፖሊሲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በAllied ቁጥጥር ስር ለሆነ ቢሮ ወይም ጣቢያ የሚሠሩ ሁሉም ሠራተኞች እንዲሁም በኩባንያው ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ያሉ ኮንትራክተሮች ይመለከታቸዋል።



ፒተር ማርሮን (Peter Marrone)
**ሊቀመንበር እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ**



ዳንኤል ራሲን (Daniel Racine)
**ፕሬዚዳንት እና ዳይሬክተር**